# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ፕላን እና ልማት ቢሮ

# በቀበሌ ደረጃ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 19/2018 ዓ.ም

## መመሪያ ቁጥር 19/2018 ዓ.ም

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# በቀበሌ ደረጃ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ያዘጋጀዉን የረጅም እና የመካከለኛ ዘመን የአሻጋሪ ዕድገትና የዘላቂ ልማት ዕቅድ ለማስፈጸም የሚያግዝ አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉና የመንግስት ዕቅድ የማህበረሰቡን ቅድሚያ ፍላጎቶች በአግባቡ ያካተተ መሆን ያለበት መሆኑ ስለታመነበት፤

ዕቅዱን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በቀበሌ ደረጃ ማህበረሰቡን በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ማሳተፍና የልማቱ ዋና ተዋናይ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ማህበረሰቡ በአካባቢው ያሉትን ፀጋዎችንና የልማት ፍላጎቶችን በመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ፣ በልማት ውጤቶች ላይ ያለውን የባለቤትነት ስሜት በማሳደግ፣ ለልማት፣ ለዴሞክራሲና ለመልካም አስተዳደር ያለውን አስተዋጽኦ ለማሻሻል፣ ከታች ወደ ላይ የዕቅድ አዘገጃጀት ሂደትን በመተግበርና ሀገራዊ ኢላማዎችን ከማህበረሰብ ፍላጎት ጋር በማጣጣም ለመተግበር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

ማህበራዊ አካቶ ትግበራን በመከወን ትኩረት ያላገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን በልማት ዕቅዶችና በውሳኔ ሂደቶች ላይ ተሳታፊ የሚያደርግና ፍትሃዊነትና ማህበራዊ ትስስርን የሚያጎለብት በመሆኑ፤

የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድን በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎችና ቀበሌዎች ወጥነትና ዘላቂነት ባለው መልኩ መተግበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ ከሀገሪቱና ከክልሉ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ጋር በተቀናጀ መልኩ በክልሉ የእድገት ማዕቀፍ መሰረት የማህበረሰቡን ተሳትፎ በዘላቂነት ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕላንና ልማት ቢሮ በተሻሻለዉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 300/2017 አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ (1) (ለ) ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በቀበሌ ደረጃ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ ቁጥር 19/2018 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **“ዕቅድ”** ማለት ከክልል እስከ ቀበሌ ባለው ደረጃ የተዘጋጀ የመንግስት ተቋማት የረጅም ዘመን፣ የመካከለኛ ወይም የአጭር ጊዜ/ዓመታዊ/ የፖሊሲ ማስፈጸሚያ ሰነድ ሆኖ ዓላማን የመንደፍ፣ ግብን የመተለም፣ የተግባራትን ቅደም ተከተል የመዘርዘር፣ ስልቶችን የመቀየስና መርሃግብር የማውጣት እንዲሁም ዓላማዎችን ለማሳካት የሚያስፈልግ የማስጸሚያ ሀብት የመመደብ ሂደት ነው፡፡

2/ **“ማህበረሰብ”** ማለት የጋራ ተቋም ያላቸው፣ የጋራ ሀብትን በጋራ የሚጠቀሙ፣ የጋራ ወግ እና እሴቶች ያላቸውን በአንድ አካባቢ የሚኖሩትን ነዋሪዎች የሚገልጽ ነው፡፡

3/ **“አሳታፊ ዕቅድ”** ማለት በተለያዩ የልማት ዕቅዶች ውስጥ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች ማለትም የወንዶችን፣ የሴቶችን፣ የወጣቶችን፣ የህጻናትን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋዊያን እና ሌሎች ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን ፍላጎቶችና ምርጫዎችን ታሳቢ ያደረገ ዕቅድ ሲሆን ይህም በማህበረሰቡ በሚወከሉ የትኩረት ቡድኖች ሙሉ ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጭነት አማካኝነት የሚከናወን ነው፡፡

4/ **“የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ”** ማለት በቀበሌ ደረጃ በማህበረሰቡ ተሳትፎ የተለዩ የልማት ፍላጎቶች ያካተተውን የዋና ዋና ዘርፎችን ዕቅድ መሰረት በማድረግ፣ በማቀናጀት እና ሀብት በመመደብ የተዘጋጀ ወጥ የሆነ የማህበረሰብ አቀፍ ዕቅድ ነው፡፡

5/ **“የትኩረት ቡድን”** ማለት በቀበሌ ደረጃ ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተወከሉ በቀበሌ ደረጃ ለሚታቀደው የልማት ዕቅድ የእያንዳንዱን ዘርፍ የሚወክሉ ቡድኖች

ሲሆኑ ማህበረሰቡን በማወያየት ኃላፊነት ወስዶ የቀበሌውን ዓመታዊ ዕቅድ የሚያቅድ ቡድን ማለት ነው፡፡

6/ **"አመቻች ቡድን"** ማለት ከአስራ ስድስት (16) እስከ አስራ ሰባት (17) አባላት ያሉት ሆኖ በቀበሌ ደረጃ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ እንዲዘጋጅ የማስተባበርና የማመቻቸት ሚና ያለው ቡድን ማለት ነው፡፡

7/ **"ዓብይ ኮሚቴ"** ማለት በወረዳ ደረጃ ባለው የአስተዳደር እርከን የሚደራጅ ሆኖ የየተቋሙን ኃላፊዎች በአባልነት ያየዘ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን በበላይነት የሚመራና የሚያስተባብር አካል ማለት ነው፡፡

8/ **"የቴክኒክ ኮሚቴ"** ማለት በወረዳ ደረጃ የሚደራጅ ቡድን ሲሆን ተጠሪነቱ ለዓብይ ኮሚቴ ሆኖ የየተቋሙን የዕቅድ ሙያተኞች በአባልነት ያካተተ ሲሆን የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበርን በቴክኒክ የሚያስተባብር፣ የሚከታተል፣ የሚደግፍ እንዲሁም አቅም የሚገነባ አካል ማለት ነው፡፡

9/ **"የማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች"** ማለት በቀበሌው ውስጥ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና በራሱ በቀበሌው ማህበረሰብ የተቋቋሙ የልማትና የመረዳጃ ማህበራት ማለት ነው፡፡

10/ **"ድጋፍ"** በዚህ መመሪያ ድጋፍ ማለት አንድ የታቀደ ዕቅድ በአግባቡ እንዲተገበር የሀሳብ፣ የእውቀትና ክህሎት እገዛ ለሚያስፈልጋቸው አካላት እገዛ ማድረግ ማለት ነው፡

11/ **"ክትትል"** ማለት ከታቀደው ዕቅድ አኳያ የሥራዎች የዕለት ከእለት እንቅስቃሴ (አፈጻጸም) የሚለካበት ሲሆን ተከታተይነት ያለው የመረጃ አሰባሰብ ሂደት እንደሆነና አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት፣ ለአጋር አካላትና ለሚመለከታቸው ሁሉ ስራው የደረሰበትን ደረጃ ለማሳወቅ፣ የተገኙ ውጤቶችን እና የሀብት አጠቃቀምን አስመልክቶ የተሟላ መረጃ በተገቢው ጊዜ የሚያደርስ የሥራ አመራር መሣሪያ ነው፡፡

12/ **"ግብረ-መልስ"** በዚህ መመሪያ ግብረ-መልስ ማለት ከድጋፍና ክትትል የተገኙ ጥንካሬዎችንና እጥረቶችን ድጋፍና ክትትል ለተደረገለት አካል በቀጣይ ጥንካሬዎችን የበለጠ አጠናክሮ እንዲቀጥል እና እጥሮቶችን እንዲቀርፍ በጽሁፍ የሚሰጥ ሀሳብ ነው፡፡

13/ **"ቢሮ"** ማለት የፕላንና ልማት ቢሮ ነው፡፡

14/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡

15/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው ሁሉ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

1/ ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በተቋቋመ ማንኛውም የመንግስት አስፈጻሚ አካል እና በሁሉም ቀበሌ ደረጃ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቅድ ተግባራትን በተመለከተ በክልሉ ውስጥ በየደረጃው የተቋቋሙት ምክር ቤቶች በዚህ መመሪያ መሰረት ስራቸውን ማከናወን ይችላሉ፡፡

## 4. የመመሪያዉ ዓላማ

1/ የቀበሌ የዕቅድ አዘገጃጀት ሂደት ማህበረሰቡን በማሳተፍና በቅድሚያ መልካም አጋጣሚዎችንና ፍላጎቶችን በመለየት፣ በዕቅድ ኡደቶች በማሳተፍ፣ የዕቅድና ልማት እንዲሁም የዕቅድ ማስፈጸሚያ ሀብት አካል የሚያደርግ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣

2/ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አሰራርን ተቋማዊ በማድረግ እና በሁሉም የክልሉ ቀበሌዎች እንዲተገበር በማስቻል በቀበሌ ደረጃ ችግር ፈች፤ ደረጃውን የጠበቀና የተቀናጀ የዕቅድ ይዘት እንዲኖር ለማድረግ፣

3/ በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት አካላት በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ሚናቸውን በግልጽ በማመላከት ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማስቻል እንዲሁም ከላይ ወደ ታች እና ከታች ወደ ላይ ያለውን የአስተቃቀድ ስነ-ዘዴ ለማመጣጠን፣

## 5. የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አዘገጃጀት መርሆዎች

የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ሲዘጋጅ የሚከተሉትን መርሆዎች መሰረት በማድረግ መከናወን ይኖርበታል፡-

1/ የተቀናጀ፣ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊነት ሂደትን መከተል

2/ የማህበረሰቡን ቅድሚያ ፍላጎቶች ማካተት፤

3/ **አካታችነት** (የትኩረት ቡድን አባላት 50(ሀምሳ) በመቶ ሴቶችና ከሁሉም ወጣቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን፣ የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ያለባቸውና ሌሎች ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች የተወከሉ መሆን አለባቸው)፤

4/ የማህበረሰቡ አስተዋጽኦ ፍላጎትና አቅምን ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ፣

5/ የአገሪቱን እና የክልሉን የልማት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጅዎች ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ማድረግ፤

6/ ቀላል፣ ወጥነት ያለው እና ደረጃውን የጠበቀ ዕቅድ በቀበሌ ደረጃ እንዲኖር ማድረግ፣

# ክፍል ሁለት

# ስለ አደረጃጀት፣ የዝግጅት ቅደም ተከተል፣ አፀዳደቅ፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት

## 6. ስለ አደረጃጀት

1/ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ዝግጅት የሚከተሉት አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በወረዳ ደረጃ የሚቋቋም ዓብይ ኮሚቴ፤

ለ) በወረዳ ደረጃ የሚቋቋም የቴክኒክ ኮሚቴ፤

ሐ) በቀበሌ ደረጃ የሚቋቋም የቀበሌ አመቻች ቡድን፣

መ) በእያንዳንዱ ቀበሌ ደረጃ በየሴክተሩ ሚቋቋም የትኩረት ቡድን፣

2/ የዓብይ ኮሚቴ አባላት የፕላን እና ልማት ተቋም ኃላፊ፣ የወረዳው ጽ/ቤት ኃላፊና የሴክተር ኃላፊዎች ናቸዉ፣

3/ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የሚመለከታቸው ሴክተሮች የዕቅድ ባለሙያዎችና የፕላን እና ልማት ተቋም የቡድኑ መሪ ናቸዉ፣

3/ የቀበሌ አመቻች ቡድን አባላት ስብጥር ዝርዝር በተመለከተ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ የትኩረት ቡድን የመስክ ስራ የትግበራ ጋይድላይን ላይ የሚቀመጠው ይሆናል፡፡

4/ የትኩረት ቡድን በማህበረሰቡ የሚመረጡ/የሚወከሉ/ ከ8 እስከ 10 አባላት ያሉት ሲሆን በእያንዳንዱ የትኩረት ቡድን ውስጥ ቢያንስ 50 በመቶ ሴቶች መሆን አለባቸው፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች የትኩረት ቡድን አባል ሆነው የሚመረጡ ይሆናል፡፡

## 7. የዝግጅት ቅደም ተከተል

1/ የትኩረት ቡድን አባላት፡-

ሀ) ዓመቱን ሙሉ መረጃ ከማህበረሰቡና ከተቋማት ሊሰበስቡ ይችላሉ፣

ለ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሀ) ቢኖርም በየዓመቱ ከሚያዚያ ወር ጀምሮ አስፈላጊውን መረጃ በመያዝ ለማቀድ መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፣

ሐ) ማህበረሰቡን በማወያየት በቀበሌው ያሉ ጸጋዎችንና ተግዳሮቶችን ይለያሉ፣

መ) የቀበሌውን ዕቅድ እንዲያዘጁ በቀበሌው ሊቀመንበር አማካኝነት በይፋ እንዲገለጽ ይደረጋል፣

ሠ) የማህበረሰቡን ቅድሚያ ፍላጎቶች በመለየት ዕቅድ ያዘጋጃሉ፣

2/ በየዘርፍ ቡድኑ የተጠናቀቀውን የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ረቂቅ ሰነድ ወደ አንድ በማጠቃለል የቀበሌው የዕቅድ ሰነድ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፣

3/ የተዘጋጀው የቀበሌ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ለቀበሌው ማህበረሰብ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት እንዲዳብር ይደረጋል፣

4/ በማህበረሰቡ አስተያየት ተሰጥቶበት የዳበረው የዕቅድ ሰነድ በቀበሌ ምክር ቤት መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

5/ የጸደቀውን ዕቅድም የቀበሌ አስተዳደር፣ አመቻች ቡድኑ፣ የትኩረት ቡድን አባላትና ማህበረሰቡ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፣

6/ በቀበሌ ደረጃ የፀደቀውን የቀበሌ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ በ3 ቅጅ በማዘጋጀት በሦስት (3) ቀናት ውስጥ አንድ (1) ቅጅ ለቀበሌው፣ አንድ (1) ቅጅ ለወረዳ አስተዳደርና አንድ (1) ቅጅ ለወረዳ ፕላንና ልማት ተቋም መላክ ይኖርበታል፡፡

7/ በተጨማሪም ቀበሌ ላይ ያሉ የየሴክተሩ ተወካዮች የየራሳቸውን ዕቅድ በወረዳ ደረጃ ላሉ እናት ሴክተሮች መላክ ይኖርባቸዋል፡፡

8/ የቀበሌ ሴክተር ተወካዮች ወደ እናት ሴክተሮች የሚልኩት ዕቅድ በቀበሌ ደረጃ ከፀደቀው ዕቅድ ጋር ተመሳሳይ መሆን የሚጠበቅበት ሲሆን ቀበሌ ላይ ተወካይ የሌላቸው የወረዳ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ለወረዳ አስተዳደር ከተላከው የዕቅድ ሰነድ ላይ በመውሰድ የየተቋማቸውን ዕቅድ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፣

## 8. ስለ አቀራረብና አፀዳደቅ

1/ በቀበሌ ምክር ቤት ተገምግሞ የፀደቀው ዕቅድ ለወረዳ አስተዳደር፣ ለፕላንና ልማት ተቋም እና ለወረዳ እናት ሴክተር መ/ቤቶች ይላካል፣

2/ የወረዳው ፕላንና ልማት ተቋም ከሁሉም ቀበሌዎች የተላከውን ዕቅድ በማካተትና በማደራጀት ለወረዳው አስተዳደር ጽህፈት ቤት ይልካል፣

3/ በወረዳው ፕላንና ልማት የተዘጋጀው የተጠቃለለ የወረዳ ዕቅድ በወረዳ አስተዳደር ስራ አስፈጻሚ/ካቢኔ ቀርቦ በጥልቀት ከተገመገመ በኂላ ለወረዳው ምክር ቤት እንዲቀርብ ይደረጋል፣

4/ የወረዳ ምክር ቤትም የቀረበለትን ዕቅድ ከገመገመና አስተያየቶቹ ከተካተቱ በኂላ ያጸድቃል፡፡

5/ በወረዳ ምክር ቤት የጸደቀው ዕቅድ ለቀበሌ አስተዳደሮችና ለትኩረት ቡድን አባላት እንዲያውቁት ይላካል፣

6/ በወረዳ ምክር ቤት የጸደቀውን ወረዳዊ ዕቅድ እያንዳንዱ ቀበሌ እንዲያውቀው በማድረግ ቀበሌዎች ዕቅዳቸውን ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፣

## 9. ስለአተገባበር፣ የክትትልና ግምገማ ስርዓት

1/ በማህበረሰቡ ቅድሚያ የተሰጣቸውን ፍላጎቶች በማካተት የፀደቀውን የልማት ዕቅድ የሚመለከታቸው የወረዳና የቀበሌ ፈጻሚ አካላት የድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት ዕቅዱን ከተፈቀደው ሀብት ጋር በማጣጣም መተግበር አለባቸው፣

2/ የቀበሌና የወረዳ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች የዕቅድ አተገባበሩን በየጊዜው መከታተልና ግብረመልስ መስጠት አለባቸው፡፡

3/ የቀበሌና የወረዳ ሴክተር አስፈጻሚዎች የዕቅድ ትግበራ እንዲከናወን በማድረግ፣ በየወሩ እና በየሩብ ዓመቱ አስፈላጊውን ክትትልና ግምገማ በማካሄድና ለቀበሌና ለወረዳ ምክር ቤቶች ሪፖርት በማቅረብ አፈጻጸሙ መገምገም ይኖርበታል፣

4/ የቀበሌ ሴክተር አስፈጻሚዎች የዕቅድ አፈጻጸሙን ቢያንስ በዓመት ሁለት (2) ጊዜ ለትኩረት ቡድን አባላት ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የተቋማት እና አደረጃጀቶች ተግባርና ኃላፊነት

### 10. የቢሮውና የሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት የወል ተግባራት

1/ ዕቅዱን አጠቃሎ በማጠናቀቅ የማሳተምና የማሰራጨት ሥራ በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ ተቋማት እና የቢሮዉ መዋቅር የጋራ ተግባር ይሆናል፡፡

2/ የጸደቀውን ዕቅድ ወደ ተግባር ለማስገባትና ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ለመስጠት እንዲቻል ተቋማትና ቢሮዉ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የዕቅድ ትውውቅ ያደርጋሉ፡፡

### 11. የቀበሌ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

1/ በዕቅድ ሂደት ውስጥ የእያንዳንዱ የማህበረሰብ ክፍል ፍላጎት መካተቱን ማረጋገጥ፤

2/ ማህበረሰቡ በራሱ ፈቃድና ፍላጎት በዕቅድ ሂደት መሳተፉን መከታተል፤

3/ ዕቅዱን ማጠቃለል እንዲሁም በቀበሌ ምክር ቤት ማስጸደቅ እና የጸደቀውን ዕቅድ ለማህበረሰቡ ማሳወቅ፤

4/ የዕቅድ ሰነዱን ለወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት እና ለወረደው ፕላንና ልማት ተቋም መላክ፤

5/ ዕቅዱ ወደ ሥራ ከገባበት ቀን ጀምሮ አፈጻጸሙን እየገመገመ በየሩብ ዓመቱ ለወረዳው አስተዳደር ጽህፈት ቤትና ለፕላንና ልማት ቡድን ማቅረብ፡፡

### 12. የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1/ በክትትልና ግምገማ ሂደት ውስጥ የመስክ ምልከታ ያካሂዳል፤

2/ ከማህበረሰቡ መረጃ በመሰብሰብ ዕቅዱ በታሰበው አግባብ መከናወኑን ይከታተላል፤

3/ የቀበሌውን የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ይገመግማል፤

4/ ለምክር ቤቱ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

## 13. የቀበሌ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1/ የቀበሌውን ዕቅድ ያጸድቃል፣ ለዕቅዱ ተፈጻሚነት ተገቢውን የማስፈጸሚያ ሀብት ይመድባል፤

2/ የጸደቀውን የቀበሌ ዕቅድ አተገባበር በቋሚ ኮሚቴዎች አማካኝነት ይከታተላል፤

3/ በቀበሌዉ ቋሚ ኮሚቴ በሚቀርብለት የውሳኔ ሀሳብ መሰረት ላልተከናወኑ ተግባራት የቀበሌ አስፈጻሚውን ተጠያቂ ያደርጋል፡፡

## 14. የማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት

1/ በድርጅቶቹ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች ታቅፈው ተጠቃሚ የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የቅድሚያ ቅድሚያ ፍላጎቶች በቀበሌና በወረዳው ዕቅድ መካተታቸውን መከታተል፤

2/ በማህበሰረቡ ዕቅዶች ውስጥ የተካተቱትን የድርጅቶቹ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ውጤት መገምገምና በምክር ቤት ጉባኤዎች ማቅረብ፣

## 15. የወረዳ ፕላንና ልማት ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድን በተመለከተ፡-

1/ በየቀበሌዎች ወቅቱንና የአሰራር ስርዓቱን ጠብቆ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

2/ እያንዳንዱ ተቋም ዓመታዊ ዕቅዱን ሲያቅድ በማህረበሰቡ የተለዩ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፍላጎቶች መካተታቸውንና ማህበረሰቡ በበቂ ሁኔታ የተሳተፈባቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

3/ የወረዳውን ዕቅድ በማጠቃለል ለወረዳ አስተዳደር አቅርቦ ያስገመግማል፣

4/ የጸደቀውን ዕቅድ ከወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በጋራ ይከታተላል፣ ይገመግማል እንዲሁም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በማዘጋጀት ያቅርባል፣

5/ ለወረዳ የዕቅድ ባለሙያዎችና ለቀበሌ አመቻቾች ስልጠና ይሰጣል፣

6/ ከወረዳው ምክር ቤት ጋር በቅርበትና በቅንጅት ይሰራል፡፡

7/ የልምድ ልውውጦችን ያመቻቻል፣ ተሞክሮዎችን ይቀምራል፣ ያደራጃል፣ ያጋራል፡፡

## 16. የወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩበታል፡፡

1/ ከፕላንና ልማት ተቋም ተጠቃሎ የቀረበለትን ዕቅድ ይገመግማል፣ የየቀበሌው የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ በወረዳው ዕቅድ መካተቱን ያረጋግጣል፣

2/ በዕቅዱ ላይ አስተያየት በመስጠት እንዲዳብር ያድርጋል፤ ለወረዳ ምክር ቤት በማቅረብ ያስጸድቃል፡

3/ ለቀበሌ ዕቅድ ማስፈጸሚያ የሚውል ሀብት/በጀት/ ይመድባል፣

4/ ዕቅዱ በተገቢው መንገድ እንዲፈጸም ለየቀበሌው አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

5/ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማደራጀት ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዲሰፉ ያደርጋል፡፡

## 17. የወረዳ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የወረዳ ምክር ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩበታል፡፡

1/ የወረዳውን ዓመታዊ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ማስፈጸሚያ የሚውል ሀብት/በጀት/ መርምሮ ያጸድቃል፣

2/ የጸደቀውን የወረዳ ዕቅድ አተገባበር በቋሚ ኮሚቴዎች አማካኝነት ይከታተላል፣

3/ በቋሚ ኮሚቴው በሚቀርብለት የውሳኔ ሀሳብ መሰረት ላልተከናወኑ ተግባራት የወረዳውንና የቀበሌውን ሥራ አስፈጻሚ ተጠያቂ ያደርጋል፣

4/ ለቀበሌ አስተዳደርና ምክር ቤቶች አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

5/ ከወረዳ ፕላንና ልማት ተቋም ጋር የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድን በተመለከተ በቅንጅትና በቅርበት ይሰራል፡፡

## 18. የዞን ፕላንና ልማት መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት

1/ ለወረዳ ፕላንና ልማት ጽህፈት ቤት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

2/ ለወረዳ ፕላን ጽህፈት ቤት ባለሙያዎችና ለሴክተር ባለሙያዎች ሥልጠናዎችን ይሰጣል፣

3/ በቀበሌዎችና ወረዳዎች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለሚመለከተው አካል በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፣

4/ የልምድ ልውውጦችን ያመቻቻል፣ ተሞክሮዎችን ይቀምራል፣ ያደራጃል፣ ያጋራል፡፡

## 19. የክልል ፕላንና ልማት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

1/ የዕቅድ ዝግጅትን በተለመከተ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት ተቋማት የአቅም ግንባት ሥልጠናዎችን ይሰጣል፣

2/ የተጠቃለለ የማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ መልክዓ-ምድራዊና የሥነ-ህዝብ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይም ያውላል፣

3/ የመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማት ማህበረሰቡን ባሳተፈ መልኩ ዕቅዳቸውን እንዴት አዘጋጅተው በምን ያህል የጊዜ ገደብ ውስጥ መላክ እንዳለባቸው የዕቅድ ጥሪ ይልካል፣

4/ ከመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማት የደረሰውን መነሻ ዕቅድ ማህበረሰቡን በበቂ ደረጃ ያሳተፈ መሆኑን በመገምገም፣ አጣጥሞ በማጠቃለል፣ መድረክ በመፍጠር፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት፣ ዕቅዱን በማዳበር፣ ለአስተያየት ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት እንዲደርስ በማድረግ፣ በውይይት የዳበረው ዕቅድ በምክር ቤት እንዲጸድቅ ያደርጋል፣

5/ ዕቅዱ እንደሁኔታው በምክር ቤት ወይም በመስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀ በኋላ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ያደርጋል፣

6/ ባለፈው በጀት ዓመት የተዘጋጀውን ዕቅድ በመገምገምና በመመርመር ለቀጣይ የዕቅድ ሥርዓት መሻሻል ይረዳ ዘንድ የእያንዳንዱን ተቋም ዕቅድ በተመለከተ በድክመትና በጥንካሬ የታዩ ጉዳዮችን ያካተተ ግብረ መልስ ይሰጣል።

7/ የተጠቃለለውን ክልላዊ ዕቅድ ማሳተም፣ ማሰራጨትና ለሚመለከታቸው አካላት የዕቅድ ትውውቅ ማድረግ፣

8/ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ አኪያ የማስፈጸሚያ የማሰልጠኛ እና የመስክ አተገባበር ማንዋሎችን ያዘጋጃል፣

9/ የዕቅዱን ስራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ያሰለጥናል፣ ተሞክሮዎችን ያሰፋል።

## 20. የህብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1/ የተሰበሰበውን የዕቅድ ማስፈጸሚያ ሀብት ውጤታማ ሊያደርግ በሚችል መልኩ በልማት ዕቅዱ ቅድሚያ የተሰጣቸውን ጉዳዮችና ዘርፎች በመለየት በጀት እንዲደለድል ለሚመለከተው አካል ያቀርባል።

2/ ከማህበረሰቡ በጉልበት፣ በሙያ፣ በቁሳቁስ እና በገንዘብ ለልማት ስራ የሚሰበሰበውን እና ጥቅም ላይ የሚውለውን አስተዋጽኦ የዕቅድ ማስፈጸሚያ ሀብት አካል እንዲሆን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

3/ ከማህበረሰቡ የሚሰበሰብ ገንዘብና ቁሳቁስ በግልጽና፣ ህጋዊነትና ተጠያቂነት ባለው አግባብ ተሰብስቦ ስራ ላይ እንዲውል ይከታተላል፤ አፈጻጸሙንም ለማህበረሰቡ ያሳውቃል፡፡

4/ ከማህበረሰቡ የተገኘውን ሀብትና በመንግስት የተመደበውን በጀት አጠቃቀም በተናጠልም ሆነ በጋራ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ብክነት በሚያደርሱ አካላት ላይም ተጠያቂነት እንዲኖር ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

## 21. በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

1/ የየተቋማቸውን መረጃ ያሰባስባሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይተነትናሉ፣ ለተጠቃሚዎችም ያሠራጫሉ፡፡

2/ በዕቅድ ዝግጅት ዙሪያ በተዋረድ ላሉ አካላት ስልጠናና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናሉ፡፡

3/ ከፕላንና ልማት ቢሮ እና በየደረጃው ካሉ መዋቅሮቹ በተላከላቸው የዕቅድ ጥሪ መሠረት በተዋረድ ላሉ አካላት የዕቅድ መነሻዎችንና አቅጣጫዎችን ይሰጣሉ፣ ከታች የሚመጣውን መነሻ ዕቅድ መሠረት አድርገው የየራሳቸውን ዕቅድ ያዘጋጃሉ፣ የተዘጋጀውን ዕቅድ ለእናት መስሪያ ቤታቸውና በየደረጃው ላለ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅር በወቅቱ ይልካሉ፣

4/ የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ መነሻ ዕቅድ በተሟላ እና ጥራት ባለው መልኩ አዘጋጅተው በየደረጃው ላለ የፕላንና ልማት ቢሮ አደረጃጀት በወቅቱ ያቀርባሉ፣

5/ በየደረጃው ባለ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅር የተጠቃለለ ዕቅድ ከተዘጋጀና በውይይት ዳብሮ በሚመለከተው አካል ከጸደቀ በኋላ እንደማዕቀፍ ሆኖ ከሚያገለግለው መሪ ዕቅድ ጋር ተናባቢ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ተቋማት እንደ አስፈላጊነቱ የየራሳቸውን መነሻ ዕቅድ ማሻሻልና የመጨረሻ ቅርጽ እንዲይዝ ያደርጋሉ፣

6/ በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ህብረተሰቡንና አጋር አካላትን ማሳተፍና አስተባብሮ መምራት ይኖርባቸዋል፡፡

7/ በቀበሌ ደረጃ በሚዘጋጀው ዕቅድ ማህበረሰቡ ዋነኛ ተዋናይና ባለቤት በመሆን ለልማቱ የላቀ አበርክቶ የሚደረግበት ሁኔታ ያመቻቻሉ፣

8/ ለዕቅድ ዝግጅቱ ትኩረት በመስጠት ብቃት ያለው መዋቅር መዘርጋት፣ እንደ አስፈላጊነቱ በቂ አደረጃጀት መፍጠር፣ ብቁ ባለሙያ መመደብ እንዲሁም የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣

9/ የየሴክተራቸውን ዕቅድ ማሳተም፣ ማሰራጨትና የዕቅድ ትውውቅ ማድረግ፣

10/ በየዘርፋቸው ማህበረሰቡን በማንቃት፣ በማነቃነቅ፣ በመደገፍ እንዲሁም በማሰልጠን ማህበረሰቡ በበቂ ሁኔታ በዘርፉ ልማት እንዲሳተፍና የየዘርፉን እድገት ለማፋጠን አዎንታዊ ሚና እንዲጫዎት ማድረግ፣

11/ የዘርፉን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎች፣ ዕቅዶች፣ ስታንዳርዶች እንዲሁም አሰራሮች ለታችኛው አሰተዳደር እርከን እና ለማህበረሰቡ ማስተዋዎቅና ማስረፅ፣

12/ በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ንቅናቄ በመፍጠር ማህበረሰቡን ማነሳሳትና በባለቤትነት ስሜት ማሳተፍ፣

## 22. በወረዳ ደረጃ የሚገኝ ዓብይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1/ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ በየጊዜው እየተገናኘ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡

## 23. በወረዳ ደረጃ የሚገኝ የቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1/ የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድን በቴክኒክ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ በየጊዜው እየተገናኘ ይገመግማል፣ አቅም ይገነባል፣ ተሞክሮዋችን ያሰፋል እንዲሁም ግብረ-መልስ ይሰጣል፣

2/ መድረክ በመፍጠር በየጊዜው ስራው ያለበትን ደረጃ በተመለከተ ለዓብይ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል፣

## 24. የትኩረት ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

1/ ማህበረሰቡን በማወያየት መረጃ ይሰበስባል፣

2/ ከቀበሌው አመቻች ቡድን የሚሰጠውን መረጃ በግብዓትነት በመጠቀም የቀበሌውን ዓመታዊ ዕቅድ ያቅዳል፣

3/ በውይይት ወቅት የሚሰጡ አስተያየቶችን በግብዓትነት ተጠቅሞ ዕቅዱን ያዳብራል፣

## 25. የቀበሌ አመቻች ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

1/ የቀበሌውን የዕቅድ ዝግጅት ሂደት ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፣

2/ የቀበሌው ዕቅድ እንዴት እንደሚዘጋጅ ለትኩረት ቡድኖች ግንዛቤ ያስጨብጣል፣

3/ ለዕቅድ ዝግጅቱ በግብዓትነት የሚውሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለየትኩረት ቡድኑ ያቀርባል፣

4/ በየትኩረት ቡድኑ የታቀደውን ዕቅድ በማጠቃለል የመጨረሻ የቀበሌ የዕቅድ ሰነድ ያዘጋጃል፣

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 26. የመስክ ሥራ የትግበራ መመሪያ ስለመጠቀም

በቀበሌ ደረጃ የሚዘጋጀው የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድ ሲዘጋጅ የትኩረት ቡድን የመስክ ስራ የትግበራ ጋይድላይንን ተከትሎ በዝርዝር የተቀመጡት አደረጃጀቶችና የአሰራር ቅደም ተከተሎች መሠረት ተድርጎ በሚዘጋጅ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

## 27. የዕቅድ ክለሳ ስለማድረግ

1/ አሳማኝ በሆነ እና በበቂ ማስረጃ በማስደገፍ በሚቀርብ ጥያቄ መነሻነት በየደረጃው ለሚገኝ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅር ቀርቦ እና በሚመለከተው ውሳኔ ሰጭ አካል ሲፈቀድ ብቻ የጸደቀ ዕቅድን መከለስ ይቻላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቀባይነት የሚኖራቸው የዕቅድ ክለሳ ምክንያቶች የሚሆኑት የሚከተሉት ናቸዉ፡-

- ሀ) የፖሊሲ፣ የስትራቴጂ፣ የደንቦችና የመመሪያዎች መለወጥ ሲኖር፣
- ለ) የጊዜ ተጽዕኖ ሲኖር፣
- ሐ) የበጀት/ገንዘብ/ እጥረት፣
- መ) ተጨማሪ በጀት/ገንዘብ መገኘት፣
- ሠ) በተቋማት የሚደረጉ የመዋቅር ለውጦች፣
- ረ) ተቋማት ሲዋሃዱ ወይም ሲነጠሉ፣
- ሰ) በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት የተከለሰ ረቂቅ ዕቅድ በየደረጃው ለሚገኝ ካቢኔ እና ምክር ቤት ቀርቦ ካልጸደቀ ተቀባይነት የለውም፡፡

## 28. ስለግበረ መልስና ተጠያቂነት

1/ በዚህ መመሪያ የተገለጹ ሁኔታዎችን በሚያጓድሉ አካላት ላይ ቢሮውና የተዋረድ መዋቅሩ በሚያደርገዉ ድጋፍ፣ ክትትል እና በሚሰጠው ግብረ-መልስ ጉድለቶችን እንዲያስተካክሉ መገለጽ ይኖርበታል፣

2/ በቢሮውና በተዋረድ መዋቅሩ የሚደረገዉ ድጋፍ፣ ክትትል እና የሚሰጠው ግብረ-መልስ ኃላፊዎችን ወይም ባለሙያዎችን በግልጽ ሊያስተምርና አቅማቸውን ሊያጎለብት የሚችል ድጋፍ መሆን ይኖርበታል፣

3/ ተቋማቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) እና (2) መሰረት በሚሰጣቸዉ የድጋፍና ክትትል ግበረ መልስ አግባብ የማያስተካክሉ ከሆነ ጉዳዩ ለካቢኔ በአጀንዳነት እንዲቀርብና ውሳኔ እንዲሰጥበት ይደረጋል፣

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተሰጠ ውሳኔ የማይታረም ሆኖ ከተገኘ በየደረጃው ያለ ምክር ቤትና ቋሚ ኮሚቴም ቁጥጥር በማድረግ አስፈላጊ ነው የሚለውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፣

5/ ይህን መመሪያ ያለአግባብ የተረጎመ ወይም ከመመሪያው ውጪ የዕቅድ ሂደትን ያከናወነ ማንኛውም አካል ተጠያቂ ይሆናል፣

## 29. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## 30. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያው ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቢሮው ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 31. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ጸድቆ ከወጣበት ከታህሳስ 30 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባሕር ዳር

ታህሳስ 30 ቀን 2018 ዓ.ም

ደመቀ ቦሩ ባህሩ (ዶ/ር)

የአብክመ ፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ